# በአራት ኪሎ ሚኒሊክ ት/ቤት በሺዎች
# የሚቆጠሩ የመድረኩን ስብሰባ ተካፈሉ

አቡጊዳ

ሕዝቡ ለሙብቱና ለነጻነቱ እንዲነሳ ለመቀስቀስ፣ አንድነት/መድረኩ በአዲስ አበባ የሚያደርጋቸዉን ታላላቅ ሕዝባዊ ስብሰባዎች በመቀጠል፣ ዛሬ መጋቢት 18 ቀን 2002 ከአቶ መለስ ዜናዊ መኝታ ቤት ደጃፍ፣ አራት ኪሎ በሚገኘዉ የዳግማዊ ሚኒሊክ ትምህርት ቤት አዳራሽ ትልቅ ስብሰባ አደረገ።

የመድረኩ አመራር አባላት ወደ አዳራሹ ሲገቡ በዚያ ተቀምጦ የነበረዉና፣ ቦታ ከመጥበቡ የተነሳ የቆመዉ በሺሆች የሚቆጠር ተሰብሳቢ፣ በጭብጨባና በፊጨት የተቀበላቸዉ ሲሆን ፣ የስብሰባዉ ፖለቲካዊ ግለት፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ «ቅንጅት መንፈስ ነዉ» ያለችዉና በዘጠና ሰባት የታየዉ የሕዝቡ የነጻነት ትግል፣ ገዢዉ ፓርቲ በጠመንጃ ኃይል ለጊዜዉ ቢያዳፍነዉም፣ ሊያጠፋዉ ያልቻለ፣ እየተቀጣጠለ የመጣ ሕዝባዊ ንቅናቄ መሆኑን ያሳየ እንደነበረ በስብሰባዉ የነበሩ ይናገራሉ።

በስብሰባዉ በነበረዉ የጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜ፣ ገዢዉ ፓርቲ አስርጎ ያስገባቸዉ ሁለት ግለሰቦች ጥያቄ እንዲያቀርቡ የተፈቀደላቸዉ ሲሆን፣ ለጠየቁትም ጥያቄዎች ተገቢዉን ምላሽ እንዳገኙ ከስፍራዉ በነበሩ ዘጋቢዎቻችን ለማረጋገጥ ችለናል።

ለነዚህ ሁለት ካድረዎች ምላሽ የሰጡት አቶ ስዬ አብርሃ ጥያቄያቸዉን ከመለሱ በኋላ «እንደምታዩት እኛ ጋር በይፋ መጥታቹህ የፈለጋችሁትን ትናገራላችሁ። ትጠይቃላችሁ። ያሰራቹህ፣ የደበደባቹህ የለም። ሂዱና ለአለቆቻቹህ ይህንን እንዲያደርጉ ንገሯቸዉ። ሂዱና ጠይቋቸዉ ። ለምንድን ነዉ እንደ እኛ በይፋ በሕዝብ ፊት የማይቆሙት ? ለምን በጓዳ ይደበቃሉ ? ለምን በሕዝብ ፊት በእናንተ ፊት የሚያራምዱትን ፖለቲካ ጠቃሚ መሆኑን ከኛ ጋር በግልጽ አይከራከሩም? ለምን በተዘጋ ቤት ዉስጥ መከራከር ይፈልጋሉ ? ለምን ሕዝብን ይፈራሉ ? ሂዱና ጠይቋቸዉ ሲሉ» በገዢዉ ፓርቲና በመድረኩ መካከል ያለዉ የዲሞክራሲያዊ ባህል ምን ያህል የተራራቀ እንደሆነ፣ ገዢዉ ፓርቲም የሚያራምደዉ ግራ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ መድረኩ ከሚቀበለዉ የሊበራል ዲሞክራሲ መካከል የሰፋ ልዩነት እንዳለው አስረድተዋል።

በኢትዮጵያ አንድነት ጠንካራና ጽኑ አቋም ያለዉን የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ፣ እንዲሁም ከዚህ በፊት ያራምዱት የነበረዉን በክልልና በአንድ ብሄር ላይ ብቻ ያተኮረ ፖለቲካ ወደ ጎን በማድረግ፣ በጋራ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር፣ ለኢትዮጵያ ሉአላዊነትን አንድነት፣ ለዜጎቿ ሙብት መከበር ለመታገል የወሰኑ የብሄር ድርጅቶችን ያቀፈዉ መድረክ፣ ከመቼዉም በላይ ያለዉ ድጋፍ ስር እየሰደደና በሰፋት እየጨመረ መምጣቱንም የደረሰን ዜና ያመለክታል።

ነገ እሁድ መጋቢት 19 ቀን 2002 በአዲስ አበባ፣ ሌሎች ሶስት ሕዝባዊ ስብሰባዎች የሚደረጉ ሲሆን፣ በቅርብ ጊዜ ዉስጥም በመላዉ አገሪቱ በስፋት በቡድን በቡድን በመሆን የመድረኩ አመራር አባላት ለቅስቀሳ እንደሚሰማሩ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።